ጎሕ ቤቶች ባንክ
GOH BETOCH BANK

# የጎሕ ቤቶች ባንክ አ.ማ.
# የባለአክሲዮኖች 3ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የጉባኤ ጥሪ

በኢፌዲሪ ንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 366(1)፣ 367(1) እና 370 እንዲሁም በባንኩ መመስረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 11(2.4) እና የመተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 8(1)፣8(3) መሠረት የጎሕ ቤቶች ባንክ አክሲዮን ማህበር **የባለአክሲዮኖች 3ኛ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ህዳር 12 ቀን 2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 2:30 ጀምሮ በአዲስ አበባ ሚሊኒየም አዳራሽ** ይካሄዳል። በመሆኑም የተከበራችሁ የባንኩ ባለአክሲዮኖች በዕለቱ በጉባኤው ላይ እንድትገኙ የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪዉን ያስተላላፋል።

## 1. የባንኩ መረጃዎች

1.1. የባንኩ ስም፡- ጎሕ ቤቶች ባንክ አ.ማ.
1.2. የባንኩ ዋና መስሪያ ቤት አድራሻ፡- አ.አ. ከተማ፣ በሌ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 2፣ የቤት ቁጥር አዲስ፤ ድረ ገጽ፣ HTTPS://WWW.GOHBETBANK.COM/
1.3. የባንኩ የምዝገባ ቁጥር፡- MT/AA/3/0052524/2013
1.4. የባንኩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ (ካፒታል)፡- ብር 2,165,617,000.00
1.5. የባንኩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ (ካፒታል)፡- ብር 1,421,883,000.00

## 2. የ3ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች

2.1. የጉባኤውን አጀንዳ ማፅደቅ፣
2.2. አዳዲስ የአክሲዮን ዝውውሮችን ማፅደቅ፣
2.3. ተተኪ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሹመት ማጽደቅ፣
2.4. እ.ኤ.አ የ2023/2024 የዳይሬክተሮች ቦርድን አመታዊ ሪፖርት ማዳመጥና ውሳኔ ማሳለፍ፣
2.5. እ.ኤ.አ የ2023/2024 የውጭ ኦዲተሮችን አመታዊ የሂሳብ ሪፖርት ማዳመጥና ውሳኔ ማሳለፍ፣
2.6. እ.ኤ.አ የ2023/2024 የሂሳብ ዘመን የተጣራ ትርፍ አመዳደብ እና አከፋፈል ላይ መወያየትና ውሳኔ ማሳለፍ፣
2.7. የዳይሬክተሮች ቦርድ የ2023/2024 አመታዊ የሥራ ዋጋ እና የ2024/25 ወርሃዊ አበል መወሰን፣

## 3. ማሳሰቢያ

3.1. በጉባኤዉ ላይ መገኘት የማትችሉ ባለአክሲዮኖች ተወካዮቻችሁ ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ የተሰጠ የዉክልና ሰነድ ዋናዉን እና ፎቶ ኮፒ እንዲሁም የወካዩን ማንነት የሚገልጽ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ኮፒ በመያዝ ወይም በንግድ ሕግ አንቀጽ 377 መሠረት ጉባኤው ከመካሄዱ ከሦስት ቀን በፊት በባንኩ ዋና መ/ቤት 2ኛ ፎቅ በአካል በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ በባንኩ የተዘጋጀዉን የዉክልና ቅፅ ሞልታችሁ በመፈረም ተወካይ መሾምና ተወካዩም የዉክልና ማስረጃዉን በመያዝ የጉባኤው ተካፋይ ለመሆንና ድምጽ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን። ሆኖም አንድ ባለአክሲዮን በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በማንኛዉም ችሎታ መወከል የሚችለው አንድ ሰው ብቻ መሆኑን ናሳዉቃለን።

3.2. ባለአክሲዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባኤው ላይ ለመሳተፍ ሲመጡ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸዉን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፈቃድ ዋናዉንና ኮፒ በመያዝ በጉባኤው ላይ መሳተፍ ይችላሉ። እንዲሁም ትውልደ ኢትዮጵያዊያን የሆኑ የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው የባንኩ ባለአክሲዮኖች ትውልደ ኢትዮጵያዊያን መሆናቸዉን የሚያረጋግጥ ቀኑ ያላለፈበት መታወቂያ (ቢጫ ካርድ) ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በአክብሮት እናሳዉቃለን።

3.3. ለተጨማሪ መረጃ የባንኩ ዋና መ/ቤት 2ኛ ፎቅ የአክሲዮን አስተዳደር ክፍል በአካል በመቅረብ ወይም በስልክ ቁጥር +251-116687252 በስራ ሰአት በመደወል መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

**የጎሕ ቤቶች ባንክ አ.ማ.**
**የዳይሬክተሮች ቦርድ**